# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 51

ጥር 28 ቀን 2015 ዓም (05-02-2023)

የዛሬውን ያገር እንዴት ሰነበተች ቅንብራችንን የምናቀርበው እንደማንኛውም ጊዜ በብዙ ውዥንብርና ውጥረት ውስጥ የተዘፈቀውን የፖለቲካና ፣የማህበረሰብ ጉዳይ ከሞላ ጎደል በመፈተሽ ይሆናል። በዬቀኑ ሳይሆን በየሰዓቱና በዬደቂቃው በአገራችን የሚከሰተውን ሁሉ በዚህ የአጭር ጊዜ ስርጭታችን ለመሸፈን አይቻልም።ሆኖም ግን አንገብጋቢ የሆኑትን በዬጊዜው እያነሳን ሳንደብቅና ሳንፈራ ከመተቸትና ከማሳወቅ እንዳልዘነጋን ሁሉ የዛሬውም ቅንብራችን ያንኑ አቋማችንን የተከተለ ነው።ከአቋምና ከእምነታችን ዝንፍ ብለን እንደማናውቅም የስርጭታችን ተከታታዮች ይመሰክራሉ ብለን እናምናለን።

አሁን አገራችን ያለችበትን አደገኛና አሳሳቢ ጉዳይ ስናነሳ  በመንግሥትና በአጋሮቹ በኩል የሚፈጠሩትን አገር የማፍረስ ተግባር ለመሸፋፈን ትኩረትን ለማሳት የሚወረወሩ የተለያዩ አጀንዳዎችን ፣በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችና ስብስቦች በኩል የሚታዩ ድክመቶችን ማለትም፣ፉክክርና መጠላለፍን፣ ያለመናበብና መልክ ያልያዘ እንቅስቃሴ፣ድክመትና ጥንካሬዎችን፣ሊከተል  የሚችለውን  የመኖር ያለመኖር አደጋ  በዛሬውም ዝግጅታችን ደግመን  ለመጠቆም እንሞክራለን።

ገዝፎ የመጣው የሕወሃት ኦሮሙማ ጥምረት አገር የማፍረስ ዘመቻ ባለፉት ጊዜያቶች ከገለጽነው በላይ ፍጥነቱን እዬጨመረ መጣ እንጂ አልቀነሰም።ካፈርኩ አይመልሰኝ ያለው በሥርዓቱ የሚመራና የሚደገፈው የጥፋት ሃይል ዓላማውን በተግባር በመግለጽ ላይ ነው።አነሳሱን ባለፉት ዝግጅቶቻችን በዝርዝር ያቀረብነው ስለሆነ ወደዚያ አንመለስበትም። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ የከፈተውን የማጥፋት ዘመቻ አጠናክሮ መሄዱን ከጥር 21 ቀን 2015 ወዲህ የተከሰቱትን ብናነሳ በዚሁ ቀን በጅማ ከተማ ከሃያ ዓመት በላይ ሕዝበ ክርስቲያኑን ሲያገለግሉ ፣ሙስሊምና ክርስቲያኑን በአባትነት ሲያቀራርቡና ለሁሉም የሚጠቅም ማህበራዊ አገልግሎት ሲሰጡ፣ትምህርት ቤት ሲሠሩ፣የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሲደክሙ፣  የሰላምና የፍቅር ሐዋርያ በመሆን ክብርና ምስጋና ያገኙት አባት አቡነ እስጢፋኖስ በረጅም ጊዜ ልመናና ድካም ያሰሩትን የቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን በዕለተ ቀኗ ባርከው ለመክፈት በቦታው ለመገኘት ያደረጉት ጉዞ በመንግሥት ትዕዛዝ በተሰማሩ የጸጥታ ሃይሎች ታግደው ፣መታገድም ብቻ ሳይሆን እንደወንጀለኛ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውለው የመጡበትን ዓላማ ሳያጠናቅቁ ከሚመሩት ደብራቸውና ከሚያገለግሉት ሕዝብ ጋር ሳይገናኙ ከኖሩበት ከተማ ድንበር ጥሶ እንደገባ ወራሪ በታጠቁ የሥርዓቱ ወታደሮች እንዲመለሱ ሆነዋል።ያንን ተከትሎ በምዕመናኑ፣በካህናቱና በጠቅላላው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ብቻ ሳይሆን በሃቀኛ አገር ወዳድ ሙስሊም፣ የፕሮቴስታንትና ካቶሊክ እምነት ተከታዮች በኩል ቁጣንና ተቃውሞን ቀስቅሷል። አገር ወዳዱ የከተማው ነዋሪ ጎሳና እምነት ሳይለዬው  አደባባይ ወጥቶ የአነግ ብልጽግና መሪ የሆነውን የሥርዓቱ ቁንጮ የአብይ አህመድንና የክልል ተብዬውን መሪ የሽመልስ አብዲሳን ስም እዬጠራ ይውረድ የሚል መፈክር አሰምቷል።የኦርቶዶክስ ልጆችም በክርስቲያናዊ ስነምግባርና መዝሙር ስሜታቸውን ሲገልጹ ውለዋል። በዚህ ብቻም ሳይቆሙ በተከታታዩ ቀናት እስከዛሬዋ እለት ተቃውሟቸውን በመግለጽ ላይ ናቸው።በቀጣይ ሲኖዶሱ ለሚያስተላልፈው ጥሪ ተዘጋጅተው በመጠባበቅ ላይ ናቸው።

በማግስቱ ጥር 22 ቀንም የሩፋኤል ክብረ በዓል እለት በመሆኑ በተለያዩ ያገራችን ክፍሎች በሚገኙት የሩፋኤል ቤተክርስቲያናት በብዙ ሽህ የሚቆጠር ምዕመናን ተገኝቶ የመንግሥትን ደባና በኦርቶዶክስ

ተዋህዶ ላይ የሚያደርሰውንም ድፍረትና አገር የማፍረስ ሴራ በግልጽ ተቃውመዋል።በሁለቱም ቀናት እንዳለፈው የጥምቀተ ባሕሩ አከባበር በአረንጓዴ ቢጫና ቀይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተጥለቀለቀ ሕዝባዊ ተቃውሞ ነበር።ይህ በራሱ የሕዝቡን ቆራጥነትና አልበገሬነት የሚያሳይ የሴረኞቹን ትምክህት የሚፈታተንና የሚሰብር ሆኖ ታይቷል።ሁኔታው ከመደበውና አዘጋጅቶ ፣እውቅናም ሰጥቶ ከሾመው ማጅራት መቺ ሲኖዶስ እጅ እዬወጣ ሲሄድበት የተደናገጠው የኦነግ ብልጽግና መንግሥት በጉልበት አድባራቱን ለመያዝ ሙከራውን በወለጋ ጀምሮታል።ይህንን እንደ መደራደሪያ አድርጎ ለመጠቀም እንጂ የሚያዋጣው ሆኖ አይደለም።አለማዋጣቱንም ወደ ሲኖዶሱ ልኮ በነበረው የካቢኔው ቡድን ውጤት አልባ ሙከራ አይቶታል።

አሁን በሁለት በኩል ሙከራ በማድረግ ላይ ነው።ሕገወጡን የኦነግ ምልምል በአቶ ሳሪዎስ በእኛ አጠራር አቶ አሪዎስ የሚመራውን ሕገወጥ ሲኖዶስ የማጠናከሩን ሥራ በአንድ በኩል ፣በሌላው በኩል ደግሞ ድርድር በሚል ሽፋን ሕገወጡን ቡድን ሕጋዊ እውቅና ሰጥቶ የቋሚው ሲኖዶስ አባል ሆኖ የጀመረውን ኢትዮጵያ የምትባለዋን አገር አፍርሶ ሌላ ኦሮሚያ የሚባል አገር የማዋለድ ሥራ በውስጥ እንዲሠራ ያመቸው ዘንድ በአትሌክቲክስ የሩጫ ችሎታዋ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ለብሳ በኢትዮጵያ ስም በዓለም የአትሌክቲክስ ውድድር አሸንፋ ዝናና ክብር ያገኘችውን ፣በጎሳ ማንነቷ ትስስር የተነሳ የኦነግ የባሕልና የወረራ እዝ ማእከል ለሆነው የአባገዳ ስብስብ የበላይ ጠባቂ የሆነችውን ሻለቃ ደራርቱ ቱሉንና ቱጃሮችን ያካተተ ቡድን መስርቶ ለማስታረቅ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።ይህ ለሌባው እውቅና ሰጥቶ፣ ከተሰረቀው የንብረቱ ባለቤት ጋር በባለቤትነት ደረጃ ይደራደር እንደማለት ነው። የእነደራርቱ ኮሚቴ ለእውነት የቆመ ከሆነ፣የቤተክርስቲኗን ቀኖናና ሥርዓት የሚያውቅና የሚረዳ ከሆነ ፣ከሃብት በላይ የአገር ህልውና የሚያሳስበው ከሆነ፣በመጀመሪያ ሕገወጡን ቡድን ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቀኖናና ሕገሥርዓት የወጣ አደገኛ አካሄድ ነው በማለት አቋም ሊወስድ በተገባው ነበር። ሁለቱንም በአቻ ደረጃ ማዬት ትክክልም መፍትሔም አይሆንም።ህልውናዊ ሳይሆን ሆዳዊ ፍርደ ገምድልነት ነው። በዚህ የድፍረትና የክህደት ተልእኮ ላይ የተሰማራው ቡድን አልፎ ተርፎም ፓትሪያርኩን አቡነ ማትያስን ከሌሎቹ ጳጳሳት ነጥሎ ለማነጋገርqna ከ,ሳካለትም እጃቸውን ይዞ ወደቤተመንግሥት ለመሄድ ጥያቄ አቅርቦ ነበር።ፓትሪያርኩ ግን ከሲኖዶሱ ተለይተው ለማነጋገ እንደማይፈቅዱና ከሲኖዶሱ የተለዬ አቋም እንደሌላቸው በመግለጽ ቡድኑን አሳረው መልሰዋል።

በወሰዱት አቋም እያመሰገንን፤ በተመሳሳይም ሕጋዊ ሲኖዶሱ ያወጣውን መመሪያ ጥሶ ከተለሳለሰና በእርቅና ይቅርታ ስም ከከሃድያኑ ጋር ልደራደር ካለ እንደከሃዲያኑ የተቋሟን ቀኖና መጣስ፣ የኦርቶዶክስ ተዋህዶንና ሕዝበ ምዕመናኑን አሳልፎ መስጠት ይሆናል።አባቶቻችንን በጭራሽ አታድርጉት ፣በአቋማችሁ ጽኑ እንላለን።

የቀውሱ ፊትአውራሪ የሆነው የኦነግ ብልጽግና መሪ አብይ አህመድ አሊ የካቢኔ አባላቱን ሰብስቦ ባሰማው መግለጫ የሚመራው መንግሥት ከሴራው ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው እዬገለጸ አያይዞ ደግሞ ሁለቱም ችግራቸውን ተነጋግረው ይፍቱ፣ሁለቱም አባቶቻችን ናቸው፤ያነሱት ችግር የሚካድ አይደለም፣የኦሮሞ ሕዝብና ሌላውም በቋንቋው ትምህርቱ ስብከቱ ይድረሰው የሚል ጥያቄ ይዘው የተነሱ አባቶች ናቸው በማለት ለአማጽያኑ እውቅና ሰጥቷል።የካቢኔ አባላቱም ሆኑ የመንግሥት አካላት እጃቸውን እንዳያስገቡ በማስጠንቀቅ ፣ሰላም ሲደፈርስና ሕዝብ ሲያልቅ ምንም እንዳያደርጉ አስጠንቅቋል።የሚያሳዝነው እነዚሁ ጉደኞች በስልጣን ላይ የተቀመጡት የአገርን ሰላምና አንድነት ለማስጠበቅ፣የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስና ደህንነቱን ለማስከበር እንደሆነ፣አገር ከሌለ እነሱም በሥልጣን ላይ ሊኖሩ ብቻም ሳይሆን ለደረሰው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሊያውቁት ይገባል። ስለሆነም ለተቀመጡበት ቦታና ሃላፊነት ሲሉ የሚጠበቅባቸውን ከመሥራት እንዲቆጠቡ ሲታዘዙ

ጭጭ እርጭ ብለው መቀመጥ ሳይሆን ሃላፊነት እንደሚሰማው ሚኒስትር ወይም የሥራ ሃላፊ እኔ ለዚህ አይነት ሃላፊነት ለጎደለው፣አገር አጥፊ ተግባር አልተባበርም ብለው ሥልጣናቸውን ጥለው መውጣት ይገባቸዋል።

አብይ አህመድ አሊ የካቢኔ አባላቱን ሰብስቦ በሰጠው ዲስኩር አልፎ ተርፎ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ከሁሉም የእምነት ተቋማት በላይ ተጠቃሚ ነች ሲል የሄደበት መንገድ ሌላው የእምነት ተቋም ተበድሏል የሚል መሰሪ መርዝ በመርጨት የተበድያለሁ ስሜት እንዲያድርበትና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ እንዲነሳ የሚቀሰቅስ ነበር።ለዘመናት የመንግሥት ሲሶ ንብረት ባለቤት የነበረችው ቤተክህነት ከ50 ዓመት ወዲህ ክብርና ይዞታዋን ተነጥቃ ከኖረች በኋላ የተረፉትን ንብረቷን ተከራክራ በሕጉ መሠረት የባለቤትነት እውቅና የማግኘቷን ሂደት እንደ አዲስ የብልጽግና ስጦታ አድርጎ አቅርቦታል። ከሌሎቹ እምነቶች ከሦስት እጥፍ በላይ በአነግ ብልጽግና ጊዜ መሬት ተሰጥቷታል ብሏል።ይህ በራሱ ሌሎቹን ተበዳይ አድርጎ የማቅረብና የመቀስቀስ እኩይ ዘዴ ነው።ደርግ ቀምቶ ከ45 ዓመታት በላይ መንግሥት ኪራይ ሲሰበስብባቸው የኖረውን፣ሳይታደሱ በመፈራረስ ጠርዝ ላይ ያሉትን ህንጻዎቿን መመለሱንም የችሮታ ያህል አድርጎ አቅርቦታል።እንደ ደንቡ ቢሆንማ ኖሮ መንግሥት ላለፉት አስርታት ዓመታት በኪራይ የሰበሰበውን ገንዘብ እስከነወለዱ የመመለስ ግዴታ አለበት።ቤተክህነትም በመመለሱ ብቻ የረካች እንጂ ተነፍጋ በነበረው መብቷ ላይ ያሰበችበት አይመስልም።ኪሳራውን ብትጠይቅ ሌላው ቢቀር ለህድሳት ወጭ ይረዳት ነበር።ጥያቄው ግን በኦሮሙማው አካሄድ ንብረቷ ብቻ ሳይሆን የቤተክህነቷም ህልውና በቋሚነት ተከብሮ የመኖሩ ነገር አጠራጣሪ ነው።አሁን እምነቶች ተከብረው የሚኖሩበት አገር የመኖር ያለመኖር ጥያቄ ስለሆነ ችግሩ ከንብረት በላይ ነው።

ሌላው ደግሞ በስደት የነበሩትን ፓትሪያርክና ጳጳሳት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የተነጠሉ በማስመሰል ሁለት አካላት አንድ እንዲሆኑ አደረኩኝ የሚልም ትርክት በመፍጠር እራሱንና የኦነግ መራሹን ተረኛ ቡድን የጥረቱና የስኬቱ ባለቤት፣የእርቅና የሰላም አባት አድርጎ አቅርቧል። የማይካደው ነገር ቢኖር በኢሕአዴግ ከአገራቸው በጉልበት ተገደው እንዲወጡ የተደረጉት ሕጋዊ ፓትሪያርክና ጳጳሳት ወደ አገር ቤት የመግባት ፈቃድ የመስጠቱ የመንግሥት ሃላፊነትና ግዴታ ስለሆነ ያንን አድርጓል እንጂ በአንድ ቤተክርስቲያን ቀኖናና ሥርዓት የሚመሩ የቤተ ክህነት አባቶች ያስታረቀበት ምንም ጠብ በመካከላቸው አልነበረም።ጠቡ ወያኔ በሚመራው መንግሥትና በቤተክህነት መካከል የተፈጠረ ነበር፣ የወያኔ አገዛዝ ከመውደቁ በፊት የወጡት ጳጳሳት አገር ውስጥ እንዲገቡ የተጀመረውን የረጅም ጊዜ ጥረት የኦነግ መራሹ የአብይ መንግሥት ትብብር አድርጓል። ዋናው ፓትሪያርክ አቡነ ማርቆሪዎስ ባደረባቸው ሕመም የተነሳ ተግባራቸውን ለመፈጸም ያዳገታቸው በመሆኑ ወያኔ ካስቀመጣቸው ፓትሪያርክ ከአቡነ ጳውሎስ ሞተ በኋላ የተተኩት አቡነ ማትያስ በቦታው ላይ መቀመጣቸው፣የአቡነ ማርቆሪዎስ ፓትሪያርክነትም የሚያበቃው ሲሞቱ ብቻ በመሆኑ የሁለቱ አብሮ መሆን በሁለት ፓትሪያርክ የመመራትን አሠራር የሚያረጋግጥ አይደለም።አብይ አህመድ ግን ሁለት ፓትሪያርክ መኖሩ የተለመደ አሠራር ስለሆነ የአሁኖቹም የኦነግ ሲኖዶስ በአቶ አሪዎስ ፓትሪያርክነት የሚመራው የማጅራት መቺ ጳጳሳት ቡድን ከቋሚው ሲኖዶስ ጋር ጎን ለጎን ሊሠሩ ይገባል የሚል አቋም ይዞ ሕገወጡን ሕጋዊነት እውቅና ሰጥቷል።ድጋፉን በዚህ ብቻም ሳያቆም በወለጋና በተለያዩ የኦሮሞ ክልሎች በመንግሥታዊ መዋቅር ድጋፍ ቤተክርስቲያንን እዬሰበረና ንብረት እዬቀማ፣እምቢ ያሉትን ሕጋዊ ቀሳውስት እያሰረና እያፈነ ምእመናኑን ጭምር ለከፋ ግጭትና ጦርነት በመከፋፈል ላይ ነው። ሌላው መሰሪና መርዘኛ መልእክቱ የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ በወያኔ ግፊት የትግራይ ቀሳውስት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እንገነጠላለን ብለው የገለጹበትን አጋጣሚ በማንሳት በዚያን ጊዜ ያልተነሳ ተቃውሞ አሁን እንዴት በኦሮሞ ላይ ይነሳል በማለት ከዚህ በፊት ኦሮሞ ጠል ብሎ የመደበውን ማህበረሰብ በድጋሚ ኮንኖታል።እንደ እውነቱ ከሆነ የትግራይ ቀሳውስት ፓትሪያርክም

አልሸሙም፣የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሚል ስያሜም ደርበው አልያዙም።ቢሆን ኖሮ እንደ ኤርትራው ተገንጣይ  የትግራይ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሚል መጠሪያ ይኖረው ነበር።አሁንም ቢሆን ያ ፍላጎት ተወግዷል ማለት አይደለም፤እራሱን ቀብሮ ጊዜ እዬጠበቀ መሆኑን መዘንጋት አይገባም። በአሁኑም የኦነግ ብልጽግና ድፍረት ላይ የአቋም መግለጫ አለማውጣቱ የዓላማ አንድነት መኖሩን ያሳያል።ወያኔ ትግራይን ለመገንጠል ከተሳካለት እውነቱ ቁልጭ ብሎ ይወጣል። እስከዚያ ድረስ ግን በአንድ አገር ሁለት ሲኖዶስ የለም ፣ሊኖርም አይገባም፤ ስለሆነም በኢትዮጵያ ስም ሁለት ፓትሪያርክና ሲኖዶስ ሊኖር አይችልም  የሚለውን ቀኖናና  ሕገሥርዓት የጣሰ ቡድንን  ለመከላከል አብይ አህመድ እንዳመጣው የሚገባው ይገባዋል።ይህ መሰሪ በዚህ ሳይቆም የበተነው ሌላው መርዝ ሕጋዊ ሲኖዶሱን ለመከፋፈል የሄደበት መንገድ ነው።አቡነ ማትያስን የትግራይ ተወላጅ ሌሎቹን በተለይም በጠንካራ አቋማቸው የሚመሰገኑትን አባቶች አቡነ ጴጥሮስንና አቡነ አብርሃምን  የአማራ ተወላጅ አድርጎ በመካከላቸው  የአቋም ለውጥና ልዩነት እንዳለ በማድረግ ሌሎቹን እንደ አቡነ ማትያስ ሁኑ ሲል ለመከፋፈል ሞክሯል።ይህ ሙከራው ግን እራሱን ይበልጥ እያጋለጠው መጣ እንጂ የቆመለትን የኦነግ ዓላማ አልጠቀመውም።ጳጳሳቱ በአንድ ላይ ቆመዋል።

የአቡዳቢን የቤተክርስቲያን መሥሪያ ቦታም  በእሱ ጥረትና ድካም ያሰገኘ አድርጎ አቅርቦታል።ይህ ተሰጠ የተባለው ቦታ ቤተክርስቲያኗ እራሷ ለብዙ ጊዜ ጠይቃ ያገኘችው መሆኑን ያደረገችውን ውጣ ውረድ ማስረጃ በማቅረብ የአብይ አህመድን  ቅጥፈት ልታጋልጠው ይገባል።

በሙስሊሙ ቤተእምነት ዙሪያ ችግር እንዲፈጠርና ሕጋዊ መጅሊሱንና መሪውን ሐጂ ሙፍቲ ኡመርን አባሮ ካሩሲ በመጣ የኦነግ ቃልቻና ተባባሪዎቹ የመተካቱንም ወንጀል እንደ መፍትሔ ጥበብ አድርጎ አቅርቦታል።እንደ እውነቱ ግን ችግሩ ይበልጥ እያደገ መጣ እንጂ አልተወገደም።

የተገንጣዩ ቡድን  ከኦነግ ፖለቲካዊ ተልእኮ በተጨማሪ ሌላው ምክንያቱ ሥጋዊ የንዋይ ጥያቄ እንጂ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ አለመሆኑን የሚያረጋግጠው የአዲስ አበባ፣የቁልቢና የደብረሊባኖስ የስለት ገቢ ለእኛ ይሰጠን ሲሉ ከተማዎቹንና ገዳማቱ ያሉበት ቦታዎች የኦሮሞ ናቸው ከሚለው የኦነግ የፖለቲካ ህሳቤ የመጣ ጠባብና ኋላ ቀር፣እራስ ወዳድና ስግብግብነት የወለደው አመለካከት ነው።

ቋንቋውንም በተመለከተ ቤተክህነት በምትችለው  መጠን በተለያዩ ቋንቋዎች ለመድረስ ሞክራለች። መጽሐፍት ተርጉማለች።እነሱንም በማካተት እንዲያስተምሩ መድባለች።ከኦነግ በተሻለ ደረጃ ብዙ መጽሃፍት በኦሮሞኛ ተርጉማ አቅርባለች።ሰባኪያንን አሰማርታ አስተምራለች።ግን በቂ ነው አይባልም። ሌሎቹም ድክመቶች እንዲሁ መኖራቸው አይካድም።ድክመትማ ባይኖርባት ኖሮ እንዲህ ቀውስ ውስጥ የሚከቱ፣ከሃዲና አስመሳይ ጳጳሳትንና ካህናትን አቅፋ ባልኖረች ነበር።ድክመት ባይኖርባትማ ኖሮ በጎቿ ከብብቷ ወጥተው በመኮብለል በሌሎች እምነቶች ውስጥ ባልገቡባት ነበር፣በአክራሪ ጅሃዲስቶች ባልታረዱባት ነበር።አሁን ፈጦ የመጣው ችግር ግን ህልውናዋን የሚነካ ነው።ይህንን ከባድና ትልቅ ፈተና በትግል ካለፈች በኋላ ሌሎቹን ውስጣዊ ችግርና ድክመቶች እንደምታስወግደው አንጠራጠርም። ለሥጋዊ ምቾት የሚሽቀዳደሙትን ፣ ለመልካም ስነምግባር ምሳሌና ምልክት ያልሆኑትንም  መክራና ቀጥታ ቤቷን ታጸዳለች የሚል የጸና እምነት አለን።

ሕጋዊው ሲኖዶስ ለኦነጉ መሪ ለአብይ አህመድ መግለጫ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል፤ያንን ተከትሎ በውስጥም በውጭም የሚኖረው ከጎኗ የቆመው ምእመን ሕዝብ  ከሃዲያኑን በመቃወምና ቤተክርስቲያኗን በመደገፍ በአደባባይ ወጥቶ ድምጹን አሰምቷል፣እያሰማም ነው።በአሜሪካ በዋሽንግተን፣በኒውዮርክ፣በካሊፎርኒያና በሌሎቹም ከተማዎች በአገር ውስጥ በሃረር፤በጅማ፣ በሻሼመኒ፣በቦንጋ፣በወሊጋ፣በአዲስ አበባ፣ በጎንደር፣በባሕርዳር፣ በደሴ፣ በደብረብርሃን፣በናዝሬት

በዝዋይ፣በኢሉባቦር፣በጋምቤላ በቀሩትም ያገሪቱ ክፍሎች በአደባባይ ወጥቶ ለአነጋውያኑና ለህወሃትያውያኑ ተቃውሞውን፣ ለሕጋዊው ሲኖዶስ ድጋፉን ገልጿል፤በመግለጽም ላይ ነው። ከዓለም የኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት በኩልም ለሕጋዊው ሲኖዶሱ የድጋፍና የአብሮነት መግለጫዎች ተልከዋል። ከነዚያም ውስጥ፣የሕንድ፣የአርመን፣የግሪክ፣የግብጽ፣የሩስያ፣የኤርትራ ግንባር ቀደሞቹ ናቸው።የበቀጣይም ለሚሰሩት የጋራ ተግባር ለመነጋገር በግብጽ አሌክሳንደርያ ከተማ ለመገናኘት ወስነዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሕጋዊ ሲኖዶስ በጥር 26 ቀን 2015 ዓም ባወጣው መመሪያ ከሰኞ ከጥር 29 ቀን ጀምሮ እስከ እሮብ የካቲት 1 ቀን 2015 ዓም ድረስ ለሦስት ቀናት ጥቁር ልብስ በመልበስ ጾምና ማህሌት እንዲደረግ ለምእመናኑ ጥሪ አድርጓል።በዚህ የተደናገጠው የኦነግ ብልጽግና ቡድን ከኦሮሚያ ክልል ብዙ የታጠቀ ሃይል ወደ አዲስ አበባ በማስጠጋትና ከተማዋን በከበባ እንደያዘ መረጃ ወጥቷል።

የኦነግ ብልጽግና ቡድን ይህንን እንደታሪካዊ አጋጣሚ በመቁጠር አሁን ወይም ሞት በሚል እብሪትና ድንፋታ በሁሉም አቅጣጫ አገር አፍርሶ አገር የመመስረቱን ጉዞ ቀጥሎበታል።ከውጭ አገር የዜና አውታሮች ጋር በመተጋገዝ የዓለም ማህበረሰቡንም በሃሰት ትርክት በማወናበድ ላይ ነው።ይህንን የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በያገሩ የሚኖሩ አገር ወዳዶችና ምሑራን በማጋለጥ ትክክለኛውን ማስረዳት ይኖርባቸዋል።

የኦነግ ብልጽግናን ቡድን አሁን ወይም በጭራሽ (NOW OR NEVERE) በሚል አቋም በወታደራዊ ሃይልና በውጭ አገር ባሰማራው የዲፕሎማሲ ክንፍ በተለያዩ ዘዴዎች ኢትዮጵያውያኑን በመከፋፈል አሁን ላለበት አቅሙን ለማጠናከር እዬጣረ ነው።ይህንን በመረዳት ኢትዮጵያኑ በረባ ባረባው መከፋፈላቸውንና በሴራ ተተብትበው እጃቸውን ከመስጠት ታቅበው የተባበሩባቸውን ጠላቶች ህወሃትንና አነጋውያኑን ከነተከታዮቻቸው ታገለው ማሸነፍ ይኖርባቸዋል።በድርድርና በመለስተኛ ጥገና ትግላቸውን ሊያቆሙ፣ትጥቃቸውን ሊፈቱ አይገባም።የሥርዓቱን ምንነት፣ከሥርዓቱ ጋር ያበሩትንና ለዚህ ደረጃ ያበቁትን የውስጥና የውጭ ጠላቶቹን ለይቶ ማወቅ አለበት፣መጀመሪያ የራሱን ቤት መፈተሽና ማጽዳት ይገባዋል።በግርግርና ለአብሮነት በሚል ሰበብ የሥርዓቱ አካልና ተጠሪ ሆኖ ለደረሰበት ሁሉ ተጠያቂ የሆነ ወንጀለኛ መልሶ የበግ ቆዳ ለብሶ በውስጡ ገብቶ እንዲያታልለው መፍቀድ አይገባም።የቄሳርን ለቄሳር ብሎ አንቅሮ ተፍቶ እውነተኛ መሪዎቹንና ወኪሎቹን መምረጥ ይኖርበታል።በሥርዓቱ ውስጥ ሆነው ወይም ሥርዓቱን ተቀብለው፣በሕገመንግሥቱ ምለው ለመከራ የዳረጉትን በፈጸሙት ወንጀል መቅጣት ሲገባ በጎሳ ማንነታቸው ብቻ የእኔ ነው ብሎ ማቀፍ ጅልነት ነው።በዚህ ፈታኝ ወቅት በግርግር የሕዝብ አሳቢ መስሎ ለመግባት የሚሽቀዳደመው ቁጥሩ ቀላል አይደለም።ከብዛት ጥራት ይሻላልና ማን ምን እንደሆነ መፈተሽና መመርመር የግድ ይላል።አለያ ትግሉ ሳይጀመር ተወለካክፎ ይቆማል።ስለሆነም ገንዘብ ወዳዱ፣ሥልጣን አሳዳጁ፣የሥርዓቱ ደጋፊና ተላላኪው ከሃቀኛው አገር ወዳድ መለዬት አለበት።አድርባይ ጋዜጠኛው፣ ምሑሩ፣ነጋዴው፣ካህኑ፣መነኩሴው ፣ ዲያቆኑና ምዕመናኑ ለፈጸመው ክህደት ንስሃ መግባት አለበት።ጥፋቱን ገልጾ ሕዝቡን ይቅርታ መጠዬቅና መካስ አለበት።ጅዋጅዌ እጫወታለሁ ብሎ ማሰብ ጊዜው ያለፈበት መሆኑን ሊረዳ ይገባል። ሕዝቡ መሮታል፣እርምጃ ከመውሰድ አይመለስምና በጊዜው የሚጠበቅባቸውን ማድረግ ከጉዳት ያተርፉቸዋል።

በቅርቡ በዋሽንግተን ከተማ ብዙ የአማራ ተወላጆች መሰብሰባቸውን ታዝበናል።መሰባሰቡ መልካምና የሚደገፍ ቢሆንም እነማን አሉበት?ያለፈው ታሪካቸው ምን ይመስላል?አሁንስ ያሰባሰባቸው ምንድን ነው? ብለን ስንመረምር ባለፈው የትግል ዘመን ገንዘብ ያባከኑና ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ፤የመንግሥትን

አቋም ሲደግፉና ሲያራምዱ የነበሩ፣አሁንም የሚያራምዱ፣ በከባቢ ልጅነት ተጠራርተው የመጡ፣ በአገርቤት ንብረትና ቤት ስለያዙ ለዚያ የሚጨነቁትንም እናገኛለን።በዚህ ውስብስብ ማንነትትና ፍላጎት ውስጥ ያሉትን እውቅና መስጠትና  በመሪነት ደረጃ ማስቀመጡ ለውድቀቱ መጀመሪያ ይሆናል።በተገለጹት ድክመቶች ውስጥ የነበሩና ያሉት ከስህተታቸው ተምረውና ይቅርታም ጠይቀው ለትግሉ በመሪነት ሳይሆን በደጋፊነት ቢቀርቡ ለነሱም ለትግሉም መልካም ይሆናል።የትግል መስክ ወይም ድርጅት መርህ ያለው እንጂ በወንዜ ልጅነት ተግበስብሰው የሚገቡበት የጎጥ ወይም የሰፈር እድር አይደለም።

 በሰሞኑ ከተሰሙት ጉዶች መካከል በጉደኛው ገዱ አንዳርጋቸውና በመሰሎቹ በነዩሃንስ ቧያለውና ጸጋዬ አራጌ በተባሉት  የወያኔ-ኦነግ አገልጋዮች ተቋቋመ የተባለው የአማራ የፖለቲካ ድርጅት አንዱ ነው።ሲጀመር የጎሳ ፖለቲካ መኖር አደገኛና አሁን ያለንበትንም አገራዊ ቀውስ ያመጣ በመሆኑ የሚያሶግዱትና የሚጠዬፉት እንጂ የሚደገፍና የሚመረጥ አይደለም።ገዱና መሰሎቹ ከጎሳ ፖለቲካ የተለዬ እውቀትና አመለካከት ሊኖራቸው አለመቻሉ የነበሩበትና አሁን አቋቋምን ያሉት ድርጅት በቂ ምስክር ነው።እነዚህ ፍትሕን የሚወክሉ፣ለፍትሕ የሚቆሙ ሳይሆኑ በፍትሕ ሚዛን ላይ ተቀምጠው በፈጸሙት ክህደትና ወንጀል ቅጣታቸውን ማግኘት ያለባቸው ወንጀለኞች ናቸው ብለን እናምናለን። ሰርቀው በሰበሰቡት ገንዘብ የአማራ ባንክ ብለው መክፈታቸው ሳያንስ አሁን የአማራ ፓርቲ ብለው መውጣታቸው ወጣቱን ገዝተው ሊያሳስቱትና ተከታይ ሊያደርጉት የሚችሉበት ጥቂትም ቢሆን የማሳሳት አቅም ሊኖራቸው ይችል ይሆናል፤ሆኖም ግን ከጥቂት ጊዜ መንፈራፈር አያልፍም። ለገንዘብ ብሎ  ወይም በጎጠኝነት ስሜት እነዚህን ከሃዲዎች የሚከተል ካለ አማሟቱ ከውሻ የረከሰ ይሆናል። በአገሩና በወገኑ ላይ የተነሳ ጠላት ተደርጎ በታሪክም በትውልድም ሲወገዝ ይኖራል።እርግጥ ነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሥርዓቱን የሚያጋልጥ ማስረጃ ማቅረባቸውና በተቃዋሚ ጎራ መሰለፋቸው አይካድም።ይህ ከሚተላለፍባቸው ቅጣት ላይ ለመቀነስ ይረዳ ይሆናል እንጂ ሙሉ ለሙሉ ምህረት እንዲያገኙ ለዚያውም በመሪነት ደረጃ ዳግም ተቀምጠው እንዲቀልዱበት የሚረዳቸው መሆን አይኖርበትም።ያ ከሆነ ለዛሬውና ለነገው ጥፋተኛ ማበረቻቻ ፣አገርና ሕዝብ በሌቦች መዳፍ ስር ስትሽከረከር እንድትኖር መፍቀድ ይሆናል።

ለአማራው ሙብት መከበር፣ለኢትዮጵያም ህልውና የጎሳ ፖለቲካ መወገድ አለበት የሚለው የጸና አቋማችን ነው።ይህ ማለት ግን አማራውም ሆነ ሌላው የሚደርስበትን ጭቆና፣መከራና ጭፍጨፋ ለመቋቋም የሚረዳ ድርጅት አይኑረው ማለት አይደለም።በሃይል የመጣበትን  ለመመከትና ብሎም ለማሶገድ የሚችል የታጠቀ ሃይል ሊኖረው ይገባል።ሃይልን በሃይል የሚለው የማይሻር አቋማችን ነው። ገዳይና አሸባሪን በልመና ወይም በፖለቲካ ፕሮግራም ብቻ የሚያሶግዱት አይሆንም።  አሁን በሚታዬው ከሆነ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብቻ የሲኖዶስ መሪ አላት።

የሕዝቡ ትግል ወሳኝ ደረጃ ላይ ደርሷል ግን መሪ የለውም።በተበታተነ መልኩ የሚገለጽ ብሶት ከመሆን አላለፈም።የፖለቲካ ድርጅት ተብዬዎቹም የሕዝቡን ትግል መምራት ቀርቶ ውስጣዊ ችግራቸውን ለማሶገድ ያልቻሉ ሆነዋል።በቅርቡ ኢዜማ  በተባለው ውስጥ የተነሳው የውስጥ ንትርክ የፖለቲካ መስመር ያመጣው ሳይሆን የጥቅም ጉዳይ የቀሰቀሰው ግብግብ ነው።ተስፋዬ ከበደ የተባለው አባሉ በብልጽግና በቦሌ ክ/ከተማ የህዳሴ ግድብ አስተባባሪ ጽ/ቤት ሹም ሆኗል የሚል ክስ ቀርቦበት ከድርጅቱ ተወግዷል።ምክንያቱን ዋጋ ቢስ የሚያደርገው የድርጅቱ መሪ ብርሃኑ ነጋ በሚኒስቴርነት ግርማ ብሩ የተባለውም ሌላው  እንዲሁ በመንግሥት የሥራ ቦታ ላይ ተቀምጠው ባለበት ሁኔታ በዚህ ሰው ላይ ብቻ ተቃውሞ መነሳቱ የዓላማ ጥሰት ያለመሆኑን ያረጋግጣል።ይህንን እንደምሳሌ አነሳን እንጂ በሌሎቹም ድርጅቶች ውስጥ በጥቅማ ጥቅም የሚካሄደው ግብግብ ቀላል አይደለም።አገር በዚህ

ቀውስ ውስጥ ስትታመስ፣የመኖር ያለመኖር ህልውናዋ ከአደጋ ላይ ሲወድቅ፣ሕዝብ በእምነቱና በጎሳ ማንነቱ ሲገደልና ሲፈናቀል የፖለቲካ ድርጅቶች ምክር ቤት የሚሉት ምንደኛ ስብስብ አንዲት መግለጫ በጋራ አላወጣም።ሌላው የኢዜማ ጉድ ይህንን ተመልክቶ ባወጣው መግለጫ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ የተከፈተውን የአነጋውያኑን ዘመቻ የሚቃወም ሳይሆን በደገፈ መልኩ የሕዝቡን ተቃውሞ መንግሥት በሃይል እንዲደፈጥጥ በጠዬቀበት መግለጫ ሕዝባዊ ተቃውሞውን አገር የማፍረስና ደም የማፋሰስ ድርጊት ነው ብሎ ተርጉሞታል።ከዚህ የበለጠ ምን አነጋዊነት፣ምን ጸረ ሕዝባዊነት፣ምንስ ጸረ ኢትዮጵያዊነት ይኖራል?

የሕዝቡ ትግል ለውጤት እንዲበቃ፣አገራችንም ከተደቀነባት አደጋ እንድትወጣ  የጋራ ግንባር መፈጠር አለበት። የጋራ ግንባሩ የፖለቲካ ና የጦር ክንፍ ያለው፣ ብሔራዊ ውህደት ያለው አመራር የሚሰጥ አካል ሊይዝ ይገባዋል።ያ በሌለበት ትግሉ ይሳካል ማለት ዘበት ነው።ጠላቶች የሚንቀሳቀሱት እነዚህን በመያዛቸው ነው።

ቤተክህነት እስከ አሁን ድረስ ሰላማዊ ትግል እያደረገች ነው። ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ቢሆንባትም ሥርዓትና ሕግ የሚያከብርና የሚያስከብር መንግሥት አለ ብላ በማመን ሕጋዊ ጥያቄ አድርጋለች። ሰሞኑን  ጥያቄዋን በሕጋዊ መንገድ የሚያቀርቡ ፈቃደኛ የሕግ ባለሙያ ጠበቆችን ያካተተ ቡድን አቋቁማ  ጉዳዩን ለፍርድ ቤት አቅርባለች።አሳሳቢ የሆነው የንብረት ምዝበራውና የቤተአድባራቱ መደፈር ጉዳይ በመሆኑ ንብረቷን ማስከበሩ ጥያቄ ቅድሚያ ተሰጥቶት በሰበር ችሎት እንዲታይላት ጥያቄ ቀርቦ ውሳኔው ለሰኞ የካቲት 29 ቀን ይጠበቃል።እንደ እኛ ግምት ከሆነ ሰበር ችሎቱ በድፍረት ንብረቷ ከሰባሪዎች ዘረፋ እንዲቆም ውሳኔ ቢያሳልፍ እንደ ቀድሞ ውሳኔዎቹ የሚያስፈጽመው አካል ተባባሪ ሊሆን እንደማይችል ጥርጣሬያችን ከፍ ያለ ነው።

ቤተክህነቷ የአገር መሥራችና ባለቤትነቷን ሳትዘነጋ ትግሏ ከንብረት በላይ መሆኑንም ማሳዬት ይኖርባታል።አገር ለማፈራረስ መንግሥታዊ መዋቅር ዘርግቶ የሚንቀሳቀሰውን  ቡድንና የጎሳ ፖለቲካውን እርኩስ ከማሪዎስ ብላ ልትታገለው ይገባል።አገር እዬፈረሰች ንብረት ሊከበር አይችልምና!

የደቡብ አሜሪካ ቀሳውስት በሰባዎቹ ዓመታት ውስጥ አገራቸው በአምባገነኖች መዳፍ ውስጥ ሲወድቁና የሕዝብ መብቶች ሲጣሱ ከመጽሃፍ ቅዱስ ጎን ለጎን የነጻነት ሃይማኖታዊ ትግል ወይም ሊብሬሽን ቴዎሎጂ የሚል መመሪያ ነድፈው፣በአንድ እጃቸው መስቀል በሌላው እጃቸው ነፍጥ ጨብጠው ታግለው አገራቸውን ከአምባገነኖች መዳፍ አላቀዋል። የዚያ አይነቱ ሰምአትነት በምድርም በሰማይም ዋጋ አለው።ክርስቶስም  ቤተመቅደሱ ሲደፈርበት ደፋሪዎቹን በጅራፍ እንደቀጣና እንዳባረረ ማሰብና መከተል ተገቢ ነው።አባቶች አገር በማዳኑና አረመኔዎችን በማስገዱ ትግል የአቡነ ጴጥሮስን ዱካ ሊከተሉ ይገባል።

የሕዝብ ሰላማዊ ትግል ብዙ መንገዶች ሲኖሩት ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

በቤት ውስጥ በመቀመጥ፣በዬቤተ እምነቱ ጸሎት በማድረግ፣ሥራ በማቆም፣በሥራ ላይ በመለገም፣ የትራንስፖርት አገልግሎት በማዛባት፣ግብር ባለመክፈል፣የመንግሥት ሚዲያ ባለማዳመጥ፣ ከመንግሥትና ከደጋፊ ነጋዴዎች የሚቀርቡትን ሸቀጦች ባለመግዛትና የሚሰጡትን አገልግሎት ባለመጠቀም፣ከውጭ አገር ገንዘብ ባለመላክ---ወዘተ የመሳሰሉትንም ያጠቃልላል።ይህ በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ ከሆነ መንግሥት ተብዬው አገር አጥፊ ቡድን ጥይት ሳይተኮስበት እጁን ይሰጣል፤ ይበታተናል።

በመከላከያና በደህንነት ተቋማት የተሰማራው ዜጋም፣ሃይማኖቱ ከሌላው ሕዝብ ያልተለዬ፣ በአገር ሃብትና በሕዝብ ገንዘብ የሚተዳደር፤ስንቅና ትጥቁም የሕዝብና ያገር ሃብት፣ሙያውም ሕዝብ ና አገር ለማገልገል መሆኑን ተረድቶ ሚናውን ለይቶ ሊቆም ይገባል።ለጥቂት እራስ ወዳዶች ጥቅምና ሥልጣን ብሎ ከሕዝብ ጋር መጣላት አይኖርበትም።እጁን በእጁ ከመቁረጥ እንዲታቀብና ሕዝባዊነቱን በተግባር እንዲገልጽ ጥሪ እናደርጋለን።

ለጋዜጠኞች የምናስተላልፈው መልእክት ቢኖር የሚሠሩበት የዜና  ተቋም የአገር ሃብትና ንብረት፣ የሚከፈላቸውም ደመወዝ ከህዝቡ ኪስ የወጣ መሆኑን ተረድተው የሚሰጡት አገልግሎት ለሕዝቡ ጥቅም ሊሆን እንደሚገባ  ሊረዱና ከመንግሥት አፈቀላጤነት ወጥተው የሕዝብ ጆሮ፣ዓይንና ልሳን እንዲሆኑ ጥሪ እናደርጋለን።አፈናና ሳንሱር የማይቃወም፣እውነቱን የሚደብቅና ሃሰት የሚነዛ ጋዜጠኛ ጋዜጠኛ አይደለም።ሙያውን  ያረከሰ ሆድ አደርና አድርባይ ነው።ከዚያም ባለፈ በሚደርሰው ሁሉ ተጠያቂ ይሆናል።የሩዋንዳውን የእልቂት መልእክት ያሰራጩውን ሃብታም  የራዲዮ ጣቢያ ባለቤት ያደረሰውን ጥፋትና  የደረሰበትን ማሰቡ መልካም ይሆናል።

አገር በዚህ ቀውስ ውስጥ እያለች ሰሞኑን የዓለም እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ባወጡት መግለጫ ከ22 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ለርሃብ አደጋ መጋለጡንና ከዚያም ውስጥ 11 ሚሊዮኑ በጠኔ ቆፈን ውስጥ እንደሚገኝ ይፋ አድርገዋል።በአገር ውስጥም የሚገኙ የእርዳታ አስተባባሪዎች ይህንኑ በተደጋጋሚ ገልጸዋል።በተለይም የፓፓዮ፣ማንጎና አቮካዶ ፣እንዲሁም የስንዴ ምርት ተትረፍርፎ ለውጭ አገሮች ለመሸጥ ተዘጋጅቻለሁ ያለው  የኦሮሞ መንግሥት ነኝ ባዩ በሚገዛው በቦረና ነገሌ ውስጥ ከ850 ሺህ ሰው በላይ ለአስከፊ ድርቅና እርሃብ ተጋልጦ ህጻናትና ደካማ አዛውንት እንዲሁም የቤት እንስሳት በማለቅ ላይ ናቸው።በቅርቡ ላለው ለዚህ እንኳን ትኩረት ያልሰጠ መንግሥት ነኝ ባይ ለሌላው ትኩረት ይሰጣል፣ሃላፊነቱን ይወጣል ብሎ መጠበቅ ጅልነት ነው።የኦሮሞ ሕዝብ በስሙ ሊጠቀምበት እንጂ ሊጠቅመው እንዳልመጣ ከዚህ ሊማር ይገባዋል።

ሕዝባዊ ትግሉ ተጀምሯል።አባቶችም በቀራንዮ መንገድ መግባታቸውን ይፋ አድርገዋል።ምእመናኑም ተከትሏቸዋል። ከአርብ ምሽት ጀምሮ በሻሸመኔና በአዲስ አበባ በመድሃኒ ዓለም ቤተክርስቲያን ግቢና ዙሪያ  ተሰባስቦ  በመዝሙርና በውዳሴ ሰላማዊ ትግሉን ሕዝቡ ተቀላቅሏል።ቤተክርስቲያናችንን አናስደፍርም ብሏል።አረመኔው የአብይ መንግሥት ሰላማው ሕዝቡን በወታደር ከቦ በጥይት መደብደብ ጀምሯል።በዚህም ወጣቶች ተገለዋል፤ቆስለዋል።ሕዝቡ ግን ንቅንቅ አላለም።ይበልጥ እልህና ቁጭት ውስጥ ገብቷል።በተለይም በሻሼመኒ ከሃዲውን ማጅራት መቺ ቡድን አጅቦ ቤተክርስቲያን ሰብሮ ለመግባት የመጣውን የታጠቀ ቡድን በባዶ እጃቸውና በመዝሙር ከሚታገሉት መሃል 35 ገሎ ብዙዎችን አቁስሎና በመቶ የሚቀጠሩትን አፍሶ ወደ አልታወቀ ቦታ መውሰዱ ይፋ ሆኗል።በሕይወት የመኖራቸው ነገር አጠራጣሪ ነው።ቤተክህነቷንም በወሮ በሎች አዘርፏል።ቅዱስ መንበሩንም አርክሷል።

 በዛሬው እለት በጥር 28 ቀን 2015 ዓም  በተጠራው አገር አቀፍ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በውስጥም በውጭም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የሌላውም እምነት ተከታይ እንደተሳተፈበት የወጡት መረጃዎች ያረጋግጣሉ።ይህ ትግል ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ አልፎ  አገራዊ መልክ ይዟል።ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አገር ነች ሲባልም ከንቱ ውዳሴ እንዳልሆነ የተረጋገጠበት የታሪክ ማህተም ሆኗል።ይህ ግን የመጨረሻው ሳይሆን የመጨረሻው መጀመሪያ ነው።የነብር ጅራት አይዙም ከያዙም አይለቁም! እስከወዲያኛው ድረስ መጓዝ ግድ ይላል።የፈራ ይመለስ!

የሰኞውን የፍርድ ቤት ውሳኔ ተከትሎ ከሲኖዶሱ የሚሰጠው ምላሽ ምን እንደሆነ ሁሉም በጉጉት ይጠብቃል።እኛም እንዲሁ።

መንግሥት ተብዬው ቡድን ብርክ ስለለቀቀበት ነገሩን በሽማግሌ ለማብረድ እዬተሯሯጠ እንደሆነ ሰምተናል።የሽምግልና ጊዜው ያለፈበት ቢሆንም ግን እራሱን ከሥልጣን ካገለለና፣ለሕዝባዊ የሽግግር መንግሥት ለማስረከብ ፈቃደኛ ከሆነ እንዳማራጭ ሊታይ ይችላል።በሥልጣን ላይ ለመቆዬትና በያዘው አገር አጥፊ መንገድ እንዲጥል የሚያደርግ ሽምግልና ከሆነ ግን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

የተቃውሞ ጎራውን የሚቀላቀሉት ቁጥራቸው እዬጨመረ መሄዱን ታዝበናል።ድምጻቸውን አጥፍተው የነበሩት የኪነት ባለሙያዎች ሳይቀሩ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጋር መቆማቸውን በመግለጽ ላይ ናቸው። የመንግሥት ሥልጣን የተሰጣቸውም እንዲሁ ከኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጋር መቆማቸውን በመግለጽ ላይ ናቸው። ከሁሉም የሚገርመው የድሬዳዋ ከንቲባና ፣የአዲስ አበባ ምክርቤት አባል የሆኑት የእስልምና እምነት ተከታይ ባለሥልጣኖች ከኦርቶዶክስ እምነት ጎን መቆማቸውን የገለጹበት መንገድ ትግሉ አገር አቀፍ የመሆኑን እድምታ ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የአብይ አህመድ የኦነግ መራሹ መንግሥት ጎራ በመናድ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ክስተት ሆኗል።ሌሎቹም ይህንን እርምጃ እንዲከተሉ ጥሪ እናደርጋለን።

ሕዝባዊ ትግሉ ይቀጥል!

የአንድነት ግንባር ይመስረት!

የጠላቶች ጎራ ይፍረስ!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር !!!